# ኢትዮጵያ የማን አገር ናት?

**በአበበ ገላው** [ጥር 30 2001]

በርካታ ኢትዮጵያዊያን ስለአገራቸው ሲናገሩና ሲጽፉ በኩራት “እምዬ ኢትዮጵያ፣ ታሪካዊቷ አገር፣የሰው ዘር መገኛ፣ የነጻነት ቀንዲል፣ የጥቁር ዘር መኩሪያ…” እያሉ ያቆላምጧታል። አባባሎቹ በሙሉ እውነታ ቢኖራቸውም፣ የኢትዮጵያ የባለቤትነት ጉዳይ ግን “እናት አገር” ብሎ በስሟ ለሚምለው ሆኖም ግን በአገሩ ባይተዋር ለሆነው አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በተግባር ያልተፈተሸ መሆኑ ብዙ ጊዜ አይወሳም።

የፋሺት ጣሊያንን ወረራ ለመመከት እጅግ ከፍተኛ የህይወት፣ የደምና የአካል መስዋእትነት የከፈለው ቡዙሃኑ ምስኪን አስታዋሽ አጥቶ ወገንና አገርን የጎዱ፣ መስዋእትነት ያልከፈሉ፣ የሸሹና የተደበቁ እንዲሁም የፋሺስቶች መንገድ መሪና ባንዳ የነበሩ ጥቂቶች ሲሾሙና ምድሪቷን በርስትነት እንደቅርጫ ሲቀራመቱ በማስተዋሉ በሃዘኔታ “እምዬ ኢትዮጵያ



ሞኝነሽ ተላላ፣ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ!” ብሎ በቁጭት ማንጎራጐሩን እየተነገረን አድገናል። የሚያሳዝነው የትናቱ እንጉርጉሮ ዛሬም በኢትዮጵያ ያለውን የባሰና የከፋ እውነታ ገላጭ ሆኖ መገኘቱ ነው።

በኢትዮጵያ ምድር፣ ያለፈውን መጥፎ የእልቂትና የግፍ ታሪክ ከማረምና ከመቀየር ይልቅ እጅግ ዘግናኝ በሆነና በከፋ ደረጃ ሲደገም ዛሬ ሀገርና ወገንን በጣም እየጎዱ ያሉ ጥቂት ወንጀለኛ ጎጠኞች አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ እትብቱ በተቀበረበት ምድር ላይ እንደ ዜጋ ሳሆን በግፍ እንደ በግ እየነዱ፣ እንዳህያ እየጫኑና እየደበደቡ፣ እንደላም እያለቡ፣ እንደፈረስ ለጉመው እየጋለቡ፣ እንደስጋ ከብት እያረዱ....በረሃብና በችግር እየቆሉ የቁም እስረኛ አድርገው አገሩን ምድራዊ ገሃነም አድርገውበት እነርሱ ጥቂቶች ግን ኢትዮጵያን ምድራዊ ገነትና የግል እርስታቸው አድርገው ለመኖር በዘር ፖለቲካ በቀየሱትን የከፋፍለህ ብላው ስልት በመጠቀም ምርጥ ምርጥ ቪላዎችን፣ የንግድ ተቋማትን፣ ሆቴሎችና መሸታ ቤቶችን እያስገነቡ ያለይሉኝታ በጥጋብ ተወጥረው እንዳህያ በመገናኛ ብዙሃን ሲያናፉ በትዝብት እናስተውላለን። ከሁሉ በላይ የሚገርመው ደግሞ አንድ ለአገርና ለወገን የሚጠቅም መልካም ስራ ሳይሰሩ ሌት ተቀን እኩይ ስራ እያከናወኑ ህዝቡን በጥላቻ መርዛቸው እየበከሉ ዘወር ብለው “የጥላቻ ፖለቲካ!” ሰለባ ሆንን ብለው ያላዝናሉ። አበው “ጅራፍ እራሱ ገርፎ አራሱ ይጮሃል!” አንደሚሉት መሆኑ ነው።

ውስብስብ ከሆነው አሳዛኙ የአገራችን ታሪክ እንደምንማረው ነገስታት ተነስተው ነገስታት ወድቀዋል፣ አሸናፊዎች ተሸንፈዋል፣ ብዙዎች ተሹመው ብዙዎች ተሽረዋል፣ ከፍ ከፍ ያሉ ሁሉ ተዋርደው ከስመዋል፣ ጥቂቶች ደልቷቸው በርዳታ ዶላር ከፈረንጆችና ከአረቦች ጥይትና ቦንብ ገዝተው ሚስኪኑን የገበሬ ልጅ በነጻነትና በአብዮት ስም በየጎራው

አሰልፈው እርስ በርስ ሲያጋድሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን የሚልሱትና የሚቀምሱት አጥተው በረሃብና በቸነፈር ከትንኞች በታች እረግፈው ቀርተዋል። የደላቸው ሲያዋጉና ደም ሲያፋስሱ፣ የሚጠባውን ጡት በረሃብ ከሞተች እናቱ አጽም ላይ ተጣብቆ ሲመጠምጥ የሚያሳይ የህጻን ምስል ባለም ዙሪያ በቴሌቪዠን ታይቶ ብዙዎችን አስለቅሶ ምንም አንኳን ሚሊዮኖች ቢያልቁም በመጨረሻ የምግብ ምጽዋት ለወገናችን ከየፈረንጅ ሀገሩ ተሰብስቦ ተላከለት። ዛሬም ለውጥ የለም፣ የድሃው ትርጉም አልባ ህይመት መቀጠያ፣ የመከራው ማራዘሚያ ከመቃብር አፋፍ ላይ ቆሞ የሚቆረጥመው የርዳታ ስንዴ ነው። “እድሜ ለነቀዳማዊ መለስ! እነርሱ በስማችን ባይለምኑ ምንበልተው ያድሩ ነበር፣ በዛ ቤተመንግስት የሚኖሩ አራዊቶች?” አንዳሉ ይነገራል አንድ አሮጊት የአራት ኪሎ የኔ ብጤ፤ ነገሩ ገብቷቸው በትዝብት በታንክ ወደተከበበው ትልቅ ግቢ ጣታቸውን ቀስረው። በርግጥ አኚህን አዛውንት የቤትመንግስቱ እልፍኝ አስከልካዮች አልሰሟቸውም እንጂ ሰምተዋቸው ቢኖን ኖሮ ወይ በእስር አለያም በአንድ ጥይት ገድለው መንግስት ግልበጣ አከሽፍን ብለው ይሸልሉ እንደነበር አያጠራጥርም፤ በአገረ ኢትዮጵያ፣ አዳኞችና ታዳኞች፣ መንታፊዎችና ተመንታፊዎች፣ በይና የበይ ተመልካቾች ተፋጠው ያሉባት ምድር። ኢትዮጵያ፣ በታሪክ ምሶሶ ላይ ተንጠልጥላ የቀረች አገር!

መሪ ተብዬዎቹ የዘመኑ ነፍሰ በሎች ካለፉት ነገስታትና መሳፍንታት ብሰው በየቤተመንግስቱና በየቪላው መሽገው በየአመቱ “ሃያ ሚሊዮን ተራበ! ሰላሳ ሚሊዮን ተጠማ! አርባ ሚሊዮን ታረዘ!” እያሉ ጠኔ ያገረጣውን፣ እረሃብ ያመነመነውን የሚስኪን ወገኖቻችንን ፎቶና ቪዲዮ ለአውሮፓና ለአሜሪካ “ለጋሾች” በዶላርና በዩሮ እየቸበቸቡ እነርሱ በድሎት ባንድ ወቅት “የዳቦ ቅርጫት” የተባለችን ሀገር አትራፊ የልመና አኩፋዳቸው አድርገዋት ስለኢኮኖሚ እድገት ይሰብኩናል። የእነርሱ ሀብትና ንብረት በሚገርም ፍጥነት በጨመረ ቁጥር ስለፈጣንና ተስፈንጣሪ የኢኮኖሚ እድገት እንደበግ ለሚያዩትና ስብእናውን በቁሙ ገፈውት ከቸነፈርና ከረሃብ ላልተላቀቀው ህዝብ ሳይታክቱ እንቅልፍ ነስተው ይደሰኩሩለታል፤ የዛሬዎቹ ነገስታት፣ የነገዎቹ የታሪክ አተሎች። ዛሬ ላይ ቆመው እየዘሩት ያለውን የታሪክ እንክርዳድ ነገ እነርሱው እንበሚሰበስቡት ማየት የተሳናቸው የውር ድንድር የዘርና የጎጥ መሳፍንታት።

ወደተነሳሁበት መሰረታዊ ጉዳይ ልመለስና አንዳንድ የሞኝ ጥያቄ ልሰንዝር። ለመሆኑ አገር ምንድነው? ስብእና ተገፈው ያለነጻነትና መብት የሚኖሩበት? እንደበግ ይሚነዱበት? የሚበላና የሚቀመስ ጠፍቶ በረሃብ፣ በጥምና በቸነፈር የሚያልቁበትና የሚሰቃዩበት? ለጥቂቶች ድሎት ግብር እየከፈሉ ተንቀውና ተዋርደው የሚኖሩበት? በጅምላ እስረኝነት ያለ እርባና ስራ አንገትን ደፍተው ይሚተክዙበት? በዘርና በቋንቋ ተከፋፍለው በጥርጣሬና በመጠላላት የሚናቆሩበት? ጥቂቶች በውሸት ሲደሰኩሩ እውነት የመተንፈስ ፈቃድ ተነፍገው ተለጉመው ያሚሰቃዩበት?...ወይንስ እንደሰው ተከብረው፣ የዜጎች መብት በማንም ወንጀላኛና ቀማኛ ሳይጣስ፣ በነጻነና በመከባብር በሰላም ያለፍርሀት የሚኖሩበት ምድር? የትኛው ነው ሀገር?

ኢትዮጵያ ብለን የምንጠራትስ ምድር የማን ንብረት ነች? የወያኔዎች? የአማሮች? የኦሮሞዎች? የአፋሮች? የሶማሌዎች፣ የኤርትራዊያን?...የመለስ ዜናዊ? የአዜብ መስፍን? የበረከት ስሞን? የስብሃት ነጋ? የአላ ሙዲን? የፕሮፌሰር መስፍን? አለም በቃኝ ለእውነት በመቆሟ የተከረቸመችው የእስረኛዋ የብርቱካን ሚደቅሳ? የቡልቻ ደምቅሳ? የስደተኛው የአባንግ ሜቶ?....የግፈኞች? ያለምንም ወንጀል በየእስርቤቱ ታጉረው ያሉ የግፍ ሰለቦች? በአገራቸው ስም በየበረሃው ሲዋጉ አይናቸው ጠፍቶ፣ እጅና አግራቸው ተቆርጦ በየመንገዱ ዳር ወድቀው “ስለእሙብርሃን አትለፉኝ!” በማለት በጣር እያቃሰቱ በሰለለ ድምጽ ዳረጎት የሚለምኑ ወገኖች? በዘርና በድርጅት ተደራጅተው ሃብት እያካበቱ፣ እየዘረፉና በጭቁኖች ስም እያምታቱ የሚኖሩ የዘመኑ ከበርቴዎችና የስዊስ ባንክ የሚስጥር ደንበኞች? የረሃብና የጥም ሰለቦች? ግፍና ችግር ቢበዛባቸው አገር ጥለው የተሰደዱት ሚሊዮኖች? ወይንስ መብታቸው ተገፎ በቁም እስር የታገቱ ጭቁን ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን? የማነች ኢትዮጵያ? ማነው ሎሌ፣ ማነው ባሪያ? ማን አሳሪ፤ ማን ታሳሪ? ማን ገዳይ፣ ማን ተገዳይ? በአገሩ፣ በመንደሩ? እኮ የማነች ኢትዮጵያ?

በመሰረቱ አገር ዜጎች ሁሉ ያለአድልኦ በኩልነት፣ መብታቸው በህግ ተጠብቆ፣ በሰላም፣ በነጻነትና በመከባበር የሚኖሩበት ምድር ካልሆነ አገርነቱ ትርጉም አልባና እራስን መሸንገያና “እኔም አገር አለኝ...” ማንጎራጎሪያ ከመሆን ሊያልፍ አለመቻሉ ብዙም አያከራክርም። ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ዛሬ በአለማችን አራቱም ማእዘናት ግፍና ችግንርን ሸሽቶ እንደፍልስጤማዊያን የተበተነው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ አገርና ወገኑን መናፈቁ ብዙም የሚያመራምር ጉዳይ አይደለም። እንደዚሁም ሁሉ ቢመረው ኢትዮጵያ ለምኔ፣ የሀበሻ ዘር አታሳዮኝ ብሎ በስደት አለም ርቆ የቀረው ስደተኛ በርካታ ሲሆን ያለውን የግፍ ስርአት ያብቃ ብሎ ብርድና ዝናብ ሳይበግረው በስደት አደባባዮች ሁሉ ተሰልፎ የተናገረ፣ የጻፈ፣ የሩቅ ድምጹን ያሰማ ሁሉ ወደ አገሩ ቢመለስ ወይ መቃብር ወይ እስር ስለሚጠብቀው ዘመዱንና ወገኑን የመጠየቅ ነጻነቱን አጥቶ አገሩን በወሮበሎች ተነጥቆ በሩቁ ባንዲራ ብቻ እያውለበለበ “እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ

ይውደም… የደፈረሽ ይውድም….” እያለ እያንጎራጎረ በስደት የቀረውም ወገን በርካታ ነው። አንድቀን አንኳን እንደሰው ተቆጥሮ ብሶቱን ሊዳምጥለት የሚከጅል ማንም የለም። በአገሩ የቀረውም ትርጉም ያጣ ህይወቱን በሃዘንና በትካዜ ይገፋል። የመናገር መብት-የእነሱ የውሸታሞቹ፣ የመገናኛ ብዙኋን-የእነርሱ ዲስኩር ማሰራጫ፣ የመደራጀት መብት-የእነርሱ የጎጥ ዛር ምርኮኞች፣ ፍርድ ቤት-የእነርሱ የፍርደ ገምድሎቹ፣ ፓርላማ-የነርሱ የጭብጨባና የሁከት መናህሸሪያ፣ ሰራዊት-የነሱ ጠባቂ… ሁሉ ቀልድ…ሁሉ የፍትህ አልበኞች መጠቀሚያ። ምስኪኑ ኢትዮጵያዊ ግን አገር አልባ ሆኖ የህይወቱን ትርጉም አጥቶ ይንከራተታል! ግን  የማንን አገር፣ ማን ይነጥቃል? ማን አባራሪ፣ ማን ተባራሪ? መልስ የሚያሻ ጥያቄ!

ደርግ የስልሳ ስድስቱን ሕዝባዊ አብዮት ጠልፎ በኪሱ ካስገባ በኋላ “ኢትዮጵያ ትቅደም፣ ያለምንም ደም!” እያለ እያዘመረ አዲሲቷን ኢትዮጵያን እንገነባለን በሚል ባዶ መርህ በርካታ ግፍ ፈጸመ። ኢትዮጵያን እንኳን እንደ አዲስ ሊገነባ ይቅንና የነበረው እንዳልነበረ ሆኖ ብዙ እልቂትና ግፍ ፈጽሞ አቧራ በላው።

ወያኔም ከሰሜን ጫፍ እስከ መሃል አዲስ አበባ በሻአቢያ ታንኮች ታጅቦ፣ አሸንጉሊት “የዘር ነጻውጪ ግንባሮችን” በአማምሳሉ ፈጥሮ እንደዶሮ ጫጨት ከኋላ እያስከተለ ከነኮተቱ ጸጉሩን አንጨፍርሮ እጁን በደም አጨማቆ አዲስ አበባ እንደገባ እርሱም በተራው “አዲሲቷ ኢትዮጵያ፣ አዲስ ምዕራፍ፣ ነጻነት ያለገደብ እስከመገንጠል…” እያለ እስከፊውን የመለስ ዜናዊን አንባገነናዊና አፋኝ ስርአት በምስኪኑ ህዝብ ጫንቃ ላይ ጫነ። ህዝቡን ከፋፈሉት፣ አናከሱት፣ አጋጩት፣ እንዳይተማመን አረጉት፣ መብቱን በሙሉ አሳጥተው እነርሱ በጎን ንግዳቸውን አጧጧፉት። ኢትዮጵያ እንኳን የእኩልነት አገር ልትሆን ይቅርና በዘር፣ በዘመድ፣ በጥቅምና በድርጅት የተሳሰሩ ጥቂት ግለሰቦች መክበሪያና መበልጽጊያ ለብዙሃኑ ደግም እስር ቤት ሆና ትገኛለች።

የመለስ ዜናዊና የጋሻ ጃግሬዎቹ ወንጀል ፀሓይ የሞቀው አለም ያወቀው ስለሆነ መደጋገሙ አስፈላጊ አይሆንም። ይሁንና ከሁሉ የከፋው ወንጀላቸው አብዛኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ በተወለደበት ምድር የሰው ክብር አጥቶ በራሱ መሬት ላይ እስረኛ ሆኖ እንደፍልስጤማዊያን የአገር አልባ ስሜት እንዲሰማው አድርገውታል። ሀገሩን የተቀማ ህዝብ!

የሌሎችን አስተሳሰብ ባልወክልም ለኔ ግን ኢትዮጵያ ገና አገሬ አይደለችም። ኢትዮጵያ ውስጥ መወልዴ ያለሙሉ የዜግነት መብት ብቻውን በቂ የዜግነት መስክር ሊሆን አይችልም። ኢትዮጵያ መሉ በሙሉ አገራችን መሆን የምትችለው ያለምንም ፍርሃት፣ በነጻነት፣ በፍትህ፣ በኩልነት፣ በሰላም፣ በአንድነትና በመከባበር መኖር ስንችል ብቻ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነው የተቃዋሚ መሪዎች ነን የሚሉ ግለሰቡች ይህንን ሀቅ ችላ በለው እርስ በርስ እየተጋጩ በጎጥ፣ በጓደኝነት፣ የአስተሳሰብ መሰሎቻተው ጋር ብቻ የሚያደርጉት ቀቢጸ ተስፋ “ትግል” የትም እንደማያደርስ በተደጋጋሚ መታየቱን ችላ ሲሉ ይስተዋላሉ። አብዛኞቹ ፓለቲከኞች መቀበል የሚገባቸው ሃቅ በስልሳዎቹ የጃጀ አስተሳሰብና የትግላ ስልት ማፍረስ ይቻል ይሆናል እንጂ አዲስ አገር አይገነባም።

የዘር፣ የጎጥ፣ የቡድንና ወገንተኛዊ ልዩነቶችን ወደጎን በመተው የጋራ አገር አንዲኖረን የጋራ እራእይ ሊኖረን ይገባል። በሺህ ያሚቆጠር የአቋም መግልጫ ከመበተንና ስብሰባ በየመንደሩ ከመጥራት አንድ የጋራ አቋም ይዞ መሰልፍ አማራጭ ይለውም። የሰላማዊ ትግል ይሁን ሌሎች አማራጮችን በህብረት ማካሄድ ወሳኝ ነው።።ያለበለዚያ እንዳሁኑ አገርን ለጠላት አስረክበን ባንዲራ ለብሰን መዞር ብቻ ይተርፈናል። “ኢትዮጵያ የማን አገር ናት?” የሚለውም መሰረታዊ ጥያቄም በአግባቡ ምላሽ የሚያገኘው ትግልን በጋራ አቀናጅቶ ጭቁን ህዝቦችን በመላ አስተባብሮ ለትግል ማነሳሳት ሲቻል ብቻ ነው።

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር!

የዚህን እውነታ ከዚህ አጭር ቪዲዮ በተግባር ማየት እንችላላን።

http://www.youtube.com/watch?v=LU8DDYz68kM

———

**abebe@stanford.edu**